# ፓልቶክ ፤ ነጻነት ዘልቆ ያልገባው ነጻ ሚዲያ

ጤና ይስጥልኝ አንባብያን፡

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ ፣ "ድሉ ዘገየ" የተባሉ ጸሃፊ "የአዛኝ ቅቤ አንጓች ወይስ አህያውን ፈርቶ ዳውላውን" በሚል አርዕስ የጻፉትን በመመርኮዝ ነው። ብዙውን ጊዜ አንድ ጸሃፊ ለሌላው ጸሃፊ ምላሽ ለማዘጋጀት የሚነሳሳው ፣ ቀድሞ የጻፈውን ሰው ሃሳብ ለመተቸት ቢሆንም ፣ እኔ ግን ይህን መጣጥፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ ፣ አቶ ድሉ ዘገየ የጻፉት ስላስደሰተኝ እና እርሳቸው በሥሱ ያነሳሱትን የፓልቶክ ፖለቲካ ይበልጥ ለመግለጽ ነው።

የድሉ ዘገየ ጽሁፍ በኢትዮሚዲያ ድህረገጽ ከተነበበ ጀምሮ ፣ ለተከታታይ ሰአታት ያለማቋረጥ በከረንት አፌርስ የመወያያ ቦታ ላይ አይነተኛ አጀንዳ መሆኑን ስገነዘብ ፣ ለአለፉት 7 አመታት የማውቀውን ፓልቶክ እንደ አዲስ እንድታዘበው አደረገኝ። ጽሁፉ ከወጣ ጀምሮ ፣ ከረንት አፌርሶች የሚወያዩት በተጻፈው ሃሳብ ዙሪያ ሳይሆን ፣ ጽሁፉን በአዘጋጁት ግለሰብ እና ጽሁፉ በተነበበት ድህረ-ገጽ "ኢትዮሚዲያ" ላይ መሆኑን ስገነዘብ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ከፉኛ አዘነሁ። ከፋኝ።

በቅድሚያ ፣ የፓልቶክ አድሚኖች ለማገናዘብ የሚሳናቸው አንድ ነገር ቢኖር ፣ ፓልቶክ የተፈጠረው በኢንተርኔት አማካኝነት ሰዎች የተለያየ ሃሳብን በድምጽ ሊያንሸራሽሩበት እንደሆነ ሁሉ ፣ እንደኢትዮሚዲያ ያሉ ግንባርቀደም የኢትዮጵያ ድህረገጾችም ፣ በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ የተለያየ ሃሳብ በጽሁፍ ሊያስተናግዱበት መሆኑን ነው። ይህንን ጽሁፍ ለሚያነብ ግለሰብ "ታዲያ የኢተርኔት ጥቅም ይሄ መሆኑን ማን ያጣዋል" የሚል አይጠፋም። ይህ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ነጻነት ምን ማለት እንደሆነ ግን ለከረንት አፌርስ አድሚኖች ሁሌ የማያገናዝቡት ጉዳይ ነው። በዚህ መወያያ ክፍል ያለምንም መሳቀቅ ሃሳብን ለመግለጽ ፡-

አንድነትን አውጋዥ ፣
መሪዎችንም ነዛናዥ
ሌላውን ሁሉ የፓልቶክ ሩምና ወያኔን በክፋት ጠሪ

አድሚኖችን አክባሪ እና እነሱን ማድመጥ እንደአስተማሪ። ግድ ይላል። እዚህ ላይ ነው ትልቁ ችግር። በእውነት ስለ እውነት የመወያያ ክፍሉ አድሚን የሚባሉት በፖለቲካ እውቀታቸውም ሆነ በስብእናቸው ከሌላው የተሻሉ ፣ አንደበታቸውም ቁጥብ የሆነ እና ሚዛናዊነትን የተካኑ ቢሆኑ ፣ እንኳንስ እንዳስተማሪ እንደፈጣሪም አምልኩን ቢሉ ምንም አልነበረም። ነገር ግን ፣ የትኛውንም አይነት የፖለቲካ ጽንሰ-ሃሳብ በአግባቡ የማስረዳት ብቃትም ሆነ ወቅታዊ የአገራችንና የአለማችንን ፖለቲካ በአግባቡ የመተቸት ሃቅማቸው በስሜት የተዋጠ ሰዎች ፣ ከሌላው ሰው የበረከተ ሰአት በፓልቶክ ማሳለፍ በመቻላቸው ብቻ ፣ የአለቃነት ካባ ደርበው ፤ ፓልቶክ ክፍላቸው ውስጥ የተለየ ሃሳብን ለማስተናገድ አለመፍቀዳቸው ብቻ ሳይሆን ፣ ሌሎች ነጻ ሚዲያዎችንም "ለምን ከኛ የተለየ ሃሳብ አስተናገዳችሁ" ብሎ ማብጠልጠል "ነውሩን የማያውቅ ወላቃ ሲስቁ ይስቃል" አይነት ይመስላል።

ከረንት አፌርሶች እንደግፋቸዋለን የሚሉት የግንቦት 7ቱ መሪ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ፣ በአውስትራሊያው ቆይታቸው ከተቹት የውይይት መድረክ አንደኛው ፓልቶክ ነው። አዎን! የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተግባራዊነትን የሚሻ እንጅ ፣ ስራ-ፈትቶ ቁጭ ብሎ ደንቁሮ በማደንቆር የሚፈታ አይደለም። ሃሳብን በቀላሉ ከመግለጫነቱ እና ትኩስ የሆኑ ሃሳቦችን በቀላሉ ለመላው አለም ለማድረስ ተስተካካይነት የሌለው ፓልቶክ ፣ በወር አንድ ቀን ነፍስ ያለው ተጋባዥ እንግዳ ይዞ ብቅ እያለ ሌላውን 29 ቀናት ግን ፍጹም ኢ-ዴሞክራሲያዊነትን የሚያስተጋባ ከሆነ ፣ የአገራችን ፖለቲካዊ ችግር ሌላው ተደራቢ ችግር ሆኖ ነው የሚቀረው።

በነጋ በጠባ አንድነትን እና መሪዎቹን ሲተቹ ውሎ ማደር ይቻላል። ግን ጥቅሙ ምንድን ነው? አንድነትን እና መሪዎቹን ሲሳሰደቡ ውሎ ማደር ይቻላል ፤ ግን የሚያስገኘው የስድብ ሽልማት ምንድን ነው?! ምንም እንኳ በሌላ ጊዜ በስፋት መመለስ የምፈልግበት ጉዳይ ቢሆንም ፣ በዳያስፖራው የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ፣ ለአገሪቱ ፖለቲካ የሚሰጠው ተጨማሪ እገዛ ይኖር እንደሆነ እንጅ የአገሪቱን ፖለቲካ ከርቀት የመዘወር ሃቅሙ በጣም ውስን ነው። አንድነት የሚታገለው የወያኔን ጫና ከኢትዮጵያ ምድር ለማቀለል እንጅ የማክዶናልን የምግብ ዋጋ ለማስቀነስ አይደለም።

በጣም የሚገርመው ፣ የአቶ ድሉ ዘገየን ጽሁፍ ተከትሎ ሌላው የከረንት አፌርስ አድሚን እና ታዳሚዎች የትችት ኢላማ የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ መሆናቸው ሲሆን ፤ እንደ አቡነዘበሰማያት የሚደገው የትችቱ አስኳልም "አቶ ስዬ የኢትዮጵያ ህዝብን ይቅርታ አልጠየቁም" የሚል ነው። ይህን ትችታቸውን ሥሰማ ለአቶ ስዬ አንድ መልዕክት ለማስተላለፍ ወደድሁ። 'እባክዎን አቶ ስዬ አብርሃ ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ ማለት ቀድሞ ስልጣን ይጋሩት የነበረውን ፓርቲ ዛሬ መታገል' መሆኑ ለአልገባቸው "ብቸኛ እና ቆራጥ የኢትዮጵያ ታጋይ የከረንት አፌርስ አድሚኖች" ይቅርታ ይጠይቁ። እነሱን ይቅርታ መጠየቅዎ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ እንደጠየቁ ይቆጠራልi ።

ሰርጸ ዳኛቸው

February 3 2010